Australian Government

Department of Immigration and Citizenship



# በጎልማሳ መጤ እንግሊዝኛ ፕሮግራም (AMEP) ውስጥ የህጻን እንክብካቤ

የጎልማሳ መጤ እንግሊዝኛ ፕሮግራም (AMEP) ለደንበኞች የህጻን እንክብካቤ መስጫ ለትምህርት የደረሰ እድሜና በ AMEP ክፍለ ትምህርት ላይ ለመሳተፍ የሚፈልግ ደንበኛ የህጻን እንክብካቤ ያቀርባል።

ለ AMEP ደንበኞች የህጻን እንክብካቤ ያለ ክፍያ ሲሰጥ፣ እንዲሁም በተቻለ መጠን ከ AMEP ደንበኞች መኖሪያ ቤት ወይም ከ AMEP መማሪያ ክፍል በ30 ደቂቃ ጉዞ እርቀት ውስጥ ይሆናል። እንደ የህጻን እንክብካቤ አካባቢ አቅርቦትና የትራንስፖርት ሁኔታ የጉዞ ጊዜው ከ30 ደቂቃ በላይ ሊሆን ይችላል።

ከመኖሪያ ቤትዎ ወይም ወደ AMEP ክፍል ለመጓዝ በ30 ደቂቃ ውስጥ እንዲሆን የርስዎ AMEP አገልግሎት አቅራቢ ለማቀናጀት ይሞክራል። ነገር ግን ይህ ሁልጊዜ ሊሳካ አይችልም። .

የህጻን እንክብካቤ የሚሰጠው እርስዎ በ AMEP ክፍለ ትምህርት ሲከታተሉ ብቻ ነው። ከርስዎ AMEP ክፍለ ትምህርት ጊዜ ውጭ ሌላ እንቅስቃሴዎችን አያካትትም።

ለርስዎ የህጻን እንክብካቤ አቅርቦት ሲገመገም፤ የርስዎ AMEP አገልግሎት አቅራቢ የተለያየ ምርጫዎችን ስለሚያቀርብልዎ ታዲያ በተቻለ ፍጥነት ትምህርትዎን ለመጀመር ይችላሉ። ለምሳሌ፡ የሚከተሉትን ሊጠየቁ ይችላሉ:

- የህጻን እንክብካቤ አቅርቦት ባለበት የማህበረሰብ ማእከል ላይ መማር
- ወደ AMEP ክፍል ለመሄድ ካልጠበቁት እርቀት በላይ መጓዝ
- የህጻን እንክብካቤ መስጫ እስከሚገኝ ድረስ በቤት ውስጥ ወይም በርቀት ትምህርት አስተማሪ መማር።

የህጻን እንክብካቤ መስጫ የተጣበበ ስለሆነ ቦታ በተሎ ላይገኝ ይችላል። ስለዚህ ከርስዎ AMEP ኮርስ ጋር በተጣጣመ የህጻን እንክብካቤ መስጫ በጊዜው የአገልግሎት አቅራቢዎች ማቀናጀት ይኖርባቸዋል።

የተቀናጀው የህጻን እንክብካቤ መስጫ የርስዎን ፍላጎት የማያሟላ ካልሆነ ይህንን ከርስዎ AMEP አገልግሎት አቅራቢ ጋር መነጋገር ነው። እንዴት ቅሬታ ስለማቅረብ ለበለጠ መረጃ እባክዎ እባክዎ ለርስዎ AMEP ማእከል የተማሪ ትንሽ መጽሐፍ ማየት ወይም ለአስተማሪዎ ወይም ለሌላ ሰራተኛ አባል ማነጋገር።

እባክዎ ያስተውሉ፤ በ AMEP ክፍል ላይ ካልተገኙ ወይም የእንግሊዝኛዎን ትምህርት ከጨረሱ ታዲያ የራስዎን የህጻን እንክብካቤ መስጫ ማቀናጀት ይኖርብዎታል።

ስለ ህጻን እንክብካቤ መስጫ በበለጠ ለማግኘት እባክዎ የርስዎን AMEP አገልግሎት አቅራቢ ያነጋግሩ።

people our business